“ጥጋብ እንዳያመን”
ሌላው ሌላው አገር፤ መብላት—ዉፍረት ቢያመው—መጥገብ ቢቸግረው፣ ስለ መብላት ቀርቶ፣ ስለ አለ-መብላት፣ ሲጠበብ ሲጨነቅ፣
አበሾች ታድለን እግዜሩ ቢወደን
ክርሰቶስ ቢያድለን
ሚኪያል ቢቀርበን
ማርያሙዋ በክንፍዋ ብታቅፍ ብትደግፈን፤
እንደ ሌላው አለም ውፍረት እንዳያመን—ጥጋብ እንዳያመን
ስለ አለ-መብላት አታስቡ ቢለን
… ሁሌም መብል የለን፤

እሰይ አላሆቹ [የዋሃቢዬ ሱፊ፣ የሱኒ የሺያ… ]
እልል እግዜሮቹ፣ የተዋህዶዎቹ [ስደተኛው ሲኖድ፣ ደግሞም ያገር ትክሉ… ] የጴንጤ እግዜሮቹ [የቃለ-ህይወቱ፣ የየሱሳዊያን፣ ደግሞም የገነቱ… አይነቱ ብዛቱ! መጤው የ‘ኢምፖርቱ’…]፤
… እግዜሮቹ… የሁሉም የአንዱም፣ የአንዱም የሁሉም… ወዘተርፈዎቹ፣ እልል… ል…. ል…. እግዜራቱ…
ጽላቱ
ደሞም መላእክቱ
ጥጋብ እንዳያመን ላረጋችሁቱ፤

ለናንተም ሹሞቹ፣ ሚጢጢ እግዜሮቹ፣ ለፓርላማዎቹ—ላዲሳባዎቹ፣
በያገር ላላችሁ—ላምባሳደሮቹ፣
መንግስት አሰኪያጆቹ፣
“ እሰይ ዕልል!” እንበል “ሹመት ያዳብርልን!”
ከፍ ከፍ ያርግልን፤ ዕድሜ ያርዝምልን፣ ውፍረት እንዳያመን ላረጋችሁቱ
እጥፍ ድርብ ይሁን ሹመት ሽልማቱ። http://www.quatero.net/archives/10343

Gelanew-kirar@hotmail.com